# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በትራንስፖርት ባለሥልጣን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደርን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

ታህሳስ/ 2006 ዓ.ም

# Contents


ክፍል 1 ..... 1
መግቢያ ..... 1
የባለስልጣን መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር ..... 1
የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ..... 4
ድርጅታዊ መዋቅር ..... 4
የሰው ኃይል ..... 4
የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ..... 4
የኦዲቱ ዓላማ ..... 4
ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ..... 5
ለከዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area) ..... 5
የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue) ..... 5
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria) ..... 6
የአሠራር ሥርዓት ትንተና መግለጫ (PROCESS DISCRIPTION) ..... 7
ክፍል ሁለት ..... 9
ግኝቶች ..... 9
2.1 የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው የተደረገ መሆኑን በተመለከተ ..... 9
የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ደህንነቱ የተጠበቀ በጊዜ፣ምቾት፣አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን በተመለከተ ..... 9
የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ቦታ መረጣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት መሆኑን በተመለከተ ..... 10
የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ ..... 14
ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለየደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን በተመለከተ፣ ..... 18
የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ  የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እና አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን አሟልተው አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ ..... 19
የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን መኖሩን በተመለከተ ..... 21
2.2 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው እያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣ ..... 23
ባለስልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ሥምሪትን ለመግታት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን  በተመለከተ ..... 23

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ የሚያደርገውን ክትትል በተመለከተ** ........ 24

2.3 ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀልጣፋ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የዘረጋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ........ 26

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ** ........ 26

**በባለስልጣን መ/ቤቱ በሚወጡ አገራዊ ደንቦች መመሪያዎችና መስፈርቶች ላይ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ** ........ 27

**የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማቋቋሙን በተመለከተ፣** ........ 28

ክፍል ሦስት ........ 29

መደምደሚያ ........ 29

ክፍል አራት ........ 32

የማሻሻያ ሃሳቦች ........ 32

አባሪ 1 የትራንስፖርት ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅር ........ 35

አባሪ ሁለት፡- ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........ 36

# ክፍል 1

## መግቢያ

1. ትራንስፖርት ለአንድ አገር ኢኮኖሚ የደም ሥር የሆነ የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ያለው የአገልግሎት ዓይነት ነው፡፡
2. በአገራችን እየተሰጠ ያለው የንግድ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘላቂነት ያለውና የኀብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ፣ ኢንቨስትመንትንና ጤናማ ውድድርን የሚያበረታታ የሕዝብን የመክፈል አቅም ያገናዘበና አቅርቦትን የሚያሳድግ ወጥ የሆነ አሠራርና አተገባበርን የሚከተል ሆኖ መከናወን ይኖርበታል፡፡
3. በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ሥራ ላይ የተሰማሩትና የሚሰሩትን ፈቃድ የሚሰጥ፣ ስምሪታቸውን የሚቆጣጠር፣ የትራንስፖርት ማህበር ሲቋቋም የሚፈቅድ፣ ለአገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብሶች በጊዜው በነበረው የአደረጃጀት ሥርዓት መሰረት ወደ 14ቱም የጠቅላይ ግዛቶች ዋና ከተሞች እንዲሰማሩ የመስመር ድልድል የሚያዘጋጅ፣ እንዲሁም ቻርተርድ ባልሆኑ ከተሞችም የከተማ ውስጥ ትራንስፖርት /የታክሲ/ አገልግሎትን የሚቆጣጠር መ/ቤት በማስፈለጉ በትዕዛዝ ቁጥር 49/1960 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 256/61 አንድ ራሱን ችሎ የሚተዳደርና ተጠሪነቱም ለፖስታ፣ ለቴሌኮሚኒኬሽንና ቴሌፎን ሚኒስቴር የሆኖ መ/ቤት ተቋቋመ፡፡ የባለሞተር ተሸከርካሪዎች ፍጥነት ወሰንን የሚሰን ደንብ ደግሞ በደንብ ቁጥር 361/1961 እንዲወጣ ተደረገ፡፡
4. ከ1966 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ በኋላ መ/ቤቱ "የመንገድ ትራንስፖርት ባለስልጣን" በመባል በአዋጅ ቁጥር 107/69 ተቋቁሟል፡፡ ተጠሪነቱም ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር እንዲሆን ተደረገ ፡፡
5. በ1983 ዓ.ም. የሽግግር መንግስት ከተመሰረተ በኋላ፣ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 14/1984 እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ከዚያም በኋላ በ1997 ዓ.ም አዲስ በወጣው አዋጅ 468/97 መሰረት መ/ቤቱ እንደ አዲስ በመዋቀር የትራንስፖርት ባለሥልጣን በመባል ተጠሪነቱ ለትራንስፖርት ሚኒስቴር (ለቀድሞው ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር) ሆኖ ተቋቁሟል፡፡

## የባለስልጣን መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

6. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ ቁጥር 468/97 መሠረት ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባር መካከል ዋና ዋናዎቹ፣

- ትራንስፖርትን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሳቦችን አዘጋጅቶ ለሚኒስትሩ ማቅረብ፤ ሲፈቀዱ ተግባራዊ ማድረግ፣
- ደህንነቱ የተረጋገጠ፤ቀልጣፋ ፤የተሟላና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት መኖሩን መከታተል፣ ትራንስፖርት የሚመለከቱ የመንግስት ፖሊሲዎችንና ህጎችን እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶች ስራ ላይ ማዋልና ማስፈፀም፣
- በአገር ደረጃና በዓለም አቀፍ የትራንስፖርት አገልግሎት መስመሮች እንዲዘረጉ ማድረግ፣
- የተቀናጀ የህዝብና የዕቃ ትራንስፖርት ስርአት እንዲስፋፋ ማድረግ፣ መንገደኞች፣ ዕቃዎችና ፖስታዎች በንግድ ትራንስፖርት ስለሚጓጓዙበት ሁኔታ መመሪያ ማውጣትና አፈፃፀሙን መከታተል፣
- ትራንስፖርትን የሚመለከቱ ማናቸውም መረጃዎችና ስታትስቲኮችን በቋሚ ሁኔታ መሰብሰብና ማጠናቀር፣
- ስለትራንስፖርት አገልግሎት እንደ አግባቡ የስልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት ፤ እንደ አስፈላጊነቱም የማሰልጠኛ ተቋሞችን ማቋቋምና ማካሄድ፣
- ትራንስፖርት በማንናቸውም ረገድ ስለሚያደግበት ሁኔታ ጥናቶች ማካሄድ ፤ እንዲካሄድ ማበረታታት እንዲሁም ፕላንና ፕሮግራም ማዘጋጀት ፤ሲፈቀድም ተግባራዊ ማደረግ፣
- በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች፤ ድርጅቶችና ማህበሮች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገልጋዩ ህብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱን ፍትሃዊ እንዲሆን ማደረግ፣ባቡሮች ስለሚወጣው ጭስ፣ጋዝና ትነት ስለመሳሰሉት ከሀገሪቱ አቅምና ከዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጋር የተገናዘበ ደረጃ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ ሲፈቀድም ተግባራዊነቱን መከታተል፣
- ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ማስወሰንና መሰብሰብ፣ በሕዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ በተሰማሩት ግለሰቦች፣ድርጅቶችና ማህበሮች የገበያ እጦት ሲያጋጥም ወይም በተገልጋዩ ሕብረተሰብ የትራንስፖርት አገልግሎት እጥረት ሲከሰት ክትትል ማድረግ ፣ እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦትና ፍላጎት መጣጣሙን ማረጋገጥና ስምሪቱ ፍትሃዊ እንዲሆን ማድረግ፣
- የቢሮዎችን አቅም ለማጎልበት አመቺ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ በመንገዶች የሚጠቀሙ ባለሞተር ተሽከርካሪዎች ከሚሰጡት አገልግሎት አይነት ሊኖራቸው የሚገባውን የደህንነት መሳሪያዎች ክብደትና መጠናቸውን እንዲሁም የተሳፋሪን ብዛትና የጭነት

ክብደትና መጠናቸውን መወሰን በዚሁ መሰረት ምዝገባ እንዲካሄድ የማረጋገጫ ሰርተፍኬት መስጠት፣

- በሀገር አቋራጭና አለም አቀፍ የንግድ የሰዎች ማመላለሻ ስራ ላይ ለሚሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች የሙያ ወይም የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠትና መከታተል፣
- በሀገር አቋራጭና በአለም አቀፍ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ የሚሰማሩ ወይም ንብረትነታቸው የዲፕሎማቲክ ፤ የአለም አቀፍ ድርጅቶች ፤ ከአንድ ክልል ወይም የፌደራል መንግስት ሆኑ ባለሞተር ተሸከርካሪዎችን መመዝገብና የቴክኒክ ምርመራ ማካሄድ እንዲሁም መከታተል፣
- በአገር አቋራጭና በዓለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ድርጅቶች ወይም ማህበራት የሚያስከፍሉትን ታሪፍ ለሚሰጡት አገልግሎት ማግኘት ስለሚገባቸው ጥቅምና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ግምት ውስት በማስገባት ማፅደቅ
- ስለተሽከርካሪዎች አመዘጋገብና የቴክኒክ ምርመራ መመሪያ ማውጣትና መከታተል፣
- ለህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚውሉ መናሀሪያዎች ደረጃና መመዘኛ (ስፔሲፊኬሽን) ማውጣትና መከታተል
- በአገር አቋራጭና በአለም አቀፍ የህዝብ ማመላለሻ ስራ ለሚሰማሩ ተሽከርካሪዎች ማህበራት የሚያቀርቡትን የስምሪት ፕሮግራም ማፅደቅ ካልቀረበለትም ራሱ ማዘጋጀትና ለዚሁ የወጣውን የዲሲፕሊን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም በገበያ ስርአት አገልግሎት እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣
- በህዝብ የንግድ የመንገድ ማመላለሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችና ድርጅቶች ፤ ማህበራት፤ የሚመለከታቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ተጠቃሚዎች የሚወከሉበት አማካሪ ኮሚቴ ማቋቋም፣ የመካከለኛ የትራንስፖርት መገልገያ መሳሪያዎች የሃገሪቷ የቦታ አቀማመጥ በሚያመች መልኩ እንዲስፋፋ ማበረታታት፣
- ለፌደራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ ከተሞችን የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማደረግ፣ የአውቶብስና ታክሲ ፌርማታዎች፣ መናሀሪያዎችና መድረሻዎች እንዲሰሩ ማድረግና ማስተዳደር

ናቸው፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

7. ባለሥልጣን መ/ቤቱ አንድ ዋና ዳይሬክተር፣ አሥር ዳይሬክቶሬት እና ሁለት (የአዲስ አበባና የድሬዳዋ) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አሉት፡፡ (ድርጅታዊ መዋቅሩ በአባሪ 1 ላይ ተያይዟል)

### የሰው ኃይል

8. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በህዳር 2006 ዓ.ም ላይ ያለው የሰው ኃይል 224 ወንድ 151 ሴት በድምሩ 375 ቋሚ እና 8 ወንድ 6 ሴት በድምሩ 14 የኮንትራት በአጠቃላይ 389 ሰራተኞች ናቸው፡፡ በትምህርት ደረጃ ሲተነተን ማንበብና መፃፍ 7 (4 ወንድ 3 ሴት) ፣ የመጀመሪያ ደረጃ 16 (11 ወንድ 5 ሴት)፣ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ 18 (17 ወንድ 1 ሴት)፣ ሁለተኛ ደረጃ 45 (23 ወንድ 22 ሴት)፣ ዲፕሎማ 168 (76 ወንድ 92 ሴት)፣ የመጀመሪያ ዲግሪ 128 (95 ወንድ 33 ሴት)፣ ሁለተኛ ዲግሪ 7 (6 ወንድ 1 ሴት) ናቸው፡፡

## የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

9. የባለሥልጣን መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ከውስጥ ከሚሰበስቡት ገቢ ሆኖ ዓመታዊ በጀቱን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በማቅረብ ሲፈቀድለት ስራ ላይ ያውላል፡፡ በዚሁ መሰረት ከ 2002 -2005 በጀት ዓመት ገቢና ወጪ በሚቀጥለው ሰንጠረዥ ላይ ተመልክቷል፡፡

| የበጀት አመት | የተሰበሰበ ገቢ በብር | የበጀት ዓመቱ ወጪ | ሥራ ላይ የዋለው በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2002 | 49,079,393.00 | 21,098452.00 | 43% |
| 2003 | 44,128,134.00 | 29,504544.00 | 67% |
| 2004 | 51,890,959.00 | 46,728622.00 | 90% |
| 2005 | 74591186.00 | 48656249.00 | 65% |

### የኦዲቱ ዓላማ

10. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የትራንስፖርት ባለሥልጣን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ሥራ በቁጠባ፣ በብቃት እና በስኬታማነት ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ

ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማቃለል የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ ነው፡፡

## ኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

11. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ደረጃዎች /EGAS/ እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን ነው፡፡ ኦዲቱ የሸፈነው ከ2002 እስከ 2005 በጀት ዓመታት እና በ2006 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የተከናወነውን የሥራ እንቅስቃሴ ነው፡፡

12. ዝርዝር ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና መስሪያ ቤት እና በባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ሁለት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች (የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የድሬዳዋ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት) እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል በክልሉ የትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ በምዕራብ አርሲ ዞን የሻሸመኔ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ እና የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል የክልሉ ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር መንገዶችና ትራንስፖርት ጽ/ቤት በመገኘት መረጃዎችን በመከለስና ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና እንዲሁም የመስክ ጉብኝት በማድረግ አሰራሩን በመመልከት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በኦዲቱ በናሙና ባልተካተቱ ስድስት የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች መጠይቆች (Survey Questionnaires) የተላከ ሲሆን ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ድረስ ከሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮ በስተቀር ሌሎቹ ምላሽ አልሰጡም፡፡

## ለክዋኔ ኦዲት የተለየው የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

13. ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ "የትራንስፖርት ባለሥልጣን የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር ተግባርን ለማከናወን የሚያስችል የአሰራር ስርዓት በቁጠባ፣ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው፡፡

## የኦዲት የትኩረት አቅጣጫ (Audit Issue)

14. ከላይ በተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ሥር ሦስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች የተመረጡ ሲሆን፣ እነርሱም ፡-

1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት

ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣

2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥምሪትን በቁጠባ፣ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን መገምገም፣
3. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀልጣፋ አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፣

የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Evaluative criteria)

15. ከላይ የተመረጡት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ለመመዘን የሚያስችሉ 30 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ በተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ላይ ሥራው የሚመለከታቸው የባለስልጣን መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች አስተያየታቸውን እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 2 ተያይዘዋል፡፡

## የአሠራር ሥርዓት ትንተና መግለጫ (PROCESS DISCRIPTION)

16. ትራንስፖርት ባለሥልጣን በማንኛውም አቅጣጫ ዘርፉን ለማሳደግ የትራንስፖርት አገልግሎት የዜጎችን ጥቅምና ፍላጎት መሰረት በማድረግ የባለሀብቱንም የልማት ተሳትፎ በማሳደግ የአሠራር ሂደቱን ለማሻሻልና የትራንስፖርቱን ሴክተር ለማሳደግ አግባብነት ካላቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመሥራት የሚከናወኑ ተግባራት የአሠራር ሂደት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**<u>የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጥ</u>**

17. የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ መሥፈርቶች እንዲዘጋጁና ወቅታዊ እንዲሆኑ በማድረግ ትክክለኛነታቸውን ያረጋግጣል፣ የአገር አቋራጭ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ ፍቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፡፡

- የሌሎች አገሮችን የተሻለ ተሞክሮ ከግምት ውስጥ ያስገባ የትራንስፖርት አደረጃጀትና የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓትን ያዘጋጃል፣ እንደሁኔታው አዳዲስ የአሰራር ስርዓትና መመሪያ ማዘጋጀትና፣ ሲፈቀድ ስራ ላይ በማዋል አፈጻጸሙን ይከታተላል፡፡
- ከአደረጃጀት፣ ከፈቃድና ምዝገባ፣ ከመናኸሪያ አጠቃቀም፣ ከስምሪት አገልግሎት ፣ ከክትትልና ድጋፍ አገልግሎት ሥራ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን ይቀበላል፣ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ ያሰጣል፡፡ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የመስመር ኔትወርኪንግ ፍላጎቶችን አጥንቶ ሲቀርብ ሥራ ላይ እንዲውል ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡
- የሥምሪት አገልግሎት ጥራቱን የጠበቀና በወጣው መስፈርትና የአሠራር መመሪያ መሠረት እየተፈፀመ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ችግሮች ሲኖሩም የመፍትሄ እርምጃ ይወስዳል፣በአጥፊ ኦፕሬተሮች ላይ የዲሲፕሊን ቅጣት ይወስናል፣ቅጣቱ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡
- የተሻለ የሥምሪት አፈፃፀም አዳዲስ የአሰራር ስልት የሚቀየስበት መንገድ እንዲጠና ያደርጋል፡፡አፈፃፀማቸውንም ይከታተላል፡፡ እንዲሁም የክልል ትራንስፖርት አደረጃጀትና አፈፃፀም ተደጋጋፊ እንዲሆንና በየጊዜው የሚጠናከርበትን ሁኔታ እንዲጠና እና እንዲተገበር ያደርጋል፡፡
- በግል በኩባንያ ወይም ተመዝግበው በማህበር ተደራጅተው የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት መስጠት የሚፈልጉ የተሸከርካሪ ባለሀብቶችን የአደረጃጀት ሞዴልና

መመሪያ ያዘጋጃል፡፡ እንዲፀድቅ በማድረግ ያደራጃል በሥራ ላይ ባለው የአሰራር ደንብ መሠረት የፈቃድ እድሳት አገልግሎት ይሰጣል፡፡

❖ ፀድቆ በሥራ ላይ ያለውን የትራንስፖርት አደረጃጀትና አገልግሎት አሰጣጥ ሕግ ባልጠበቁ ኦፕሬተሮች የሕዝብ ትራንስፖርት ማህበራትና ድርጅቶች ላይ የፈቃድ እገዳና ስረዛ ያደርጋል፡፡ በሕዝብ ትራንስፖርት ዘርፍ የሚሰማሩና የተሰማሩ ባለሙያዎችን በስልጠና ይደግፋል፡፡

❖ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች አቅም ለመገንባት ተገቢውን ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፡፡ የሕዝብ ትራንስፖርት መረጃዎችን እየሰበሰበ ጥቅም ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡ የመናህሪያዎች የአሠራር አገልግሎት ደረጃውን የጠበቀ ሆኖ እንዲራመድ ያደርጋል፣የሌሎች አገሮች የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ እንዲጠና ያደርጋል፣ ለክልል ቢሮዎችና ለትራንስፖርተሮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን ይሰራል፡፡ በመናኸሪያ አገልግሎት የሚሰጠውን ሕዝብ በተሻለ የትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆንበትን መንገድ ያስጠናል ለተግባራዊነቱም ይሰራል፡፡

❖ በመደበኛ ስምሪት ያልተሸፈኑ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚጠይቁ አካባቢዎች በአግባቡ እንዲሸፈኑ የተለያዩ አማራጮችን በማቅረብ መስመሮች የሚሸፈኑበት ሁኔታ ያመቻቻል፡፡ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አውቶብሶች በደረጃ የተለዩና የገበያ ውድድርን የሚያበረታታ ሆኖ እንዲተገበር ያደርጋል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ የኦፕሬተርስ አገልግሎት አሰጣጥ ጥራትና ሁለንተናዊ አቅም የሚያጠናክርበትን ሁኔታ ያመቻቻል ተገቢውን ድጋፍና ክትትል የሚደረግበትን መንገድ በማፈላለግ የተገልዩን ፍላጎት ያሟላ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

❖ የንግድ የሕዝብ የመንገድ ማመላለሻ መናኸሪያዎችና ማረፊያ ቦታዎች በወጣው መመዘኛ መሠረት መሠራታቸውን እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጡም ጥራቱን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ሀገራዊ የመናኸሪያ መረጃዎችን ያሰባስባል፡፡ የወጡ ደረጃዎች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግኝቶች

## 2.1 የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው የተደረገ መሆኑን በተመለከተ

### የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ደህንነቱ የተጠበቀ በጊዜ፣ምቾት፣አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ መሆኑን በተመለከተ

18. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው፣ የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በጊዜ፣ ምቾት፣ አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ሊሆን ይገባል፡፡

19. ባለስልጣን መ/ቤቱ በህዳር 2004 ዓ.ም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች የአገልግሎት አሰጣጥ በክልሎች እና በአዲስ አበባ ከሚገኙ መናኸሪያዎች የተገልጋዮችን እይታ ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት አድርጓል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው መጠይቅ ከቀረበላቸው ውስጥ በቂ አገልግሎት መስጫ ቦታ አለመኖሩን (74%)፣ የመናኸሪያ መገኛ ቦታ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ምቹ አለመሆኑ (55%)፣ መናኸሪያዎቹ የተጠቃሚውን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ የተደራጀ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ (82%)፣ መናኸሪያዎች ለአካል ጉዳተኞች ለህፃናት ለእናቶች እና ለአረጋዊያን ምቹ ሁኔታዎችን የፈጠረ አለመሆኑ (63.6%)፣ መናኸሪያዎች ለሠራተኞች ምቹ የሥራ አካባቢ ሆነው የተደራጁ አለመሆናቸው (82%)፣ መናኸሪያዎች በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ (91%)፣ በአጠቃላይ በየመናኸሪዎች የሚሰጠው አገልግሎት ተገልጋዩን የማያረካ መሆኑን (75%) መግለጻቸውን ጥናቱ ያስረዳል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረትም የተወሰደውን የዕርምት እርምጃ በተመለከተ ኦዲቱ አስከተጠናቀቀበት ድረስ ባለሥልጣኑ መረጃ አላቀረበም፡፡

20. በተጨማሪም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት የባለስልጣኑ በድሬዳዋና የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ መናኸሪያዎች፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ፣ በሐረሬ ክልል የሐረር ከተማ፣ የኦሮሚያ ክልል የአዳማ ከተማ፣ ምዕራብ አርሲ ዞን የሻሸመኔ ከተማ፣ የአዲስ አበባ አነስተኛና መለስተኛ (አዲስ ከተማ) እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ውስጥ ተመሳሳይ ሞዴል ያላቸው አነስተኛና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች እንዲጭኑ ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ተጨማሪ መቀመጫዎች

የጨመሩ፣ በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት ባለሥልጣኑ ካስቀመጠው የርቀት መጠን ያነሰ ሆኖ የተሰሩ በመኖራቸው ተጠቃሚው ሕብረተሰብ ደህንነቱንና ምቾቱ ሳይጠበቅ የሚጓዝበት ሁኔታ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ሚኒባስ ታክሲዎችና ድጋፍ ሰጪ ሚኒባሶች በወንበሮች መካከል ያለው ርቀት በደረጃው ከተቀመጠው ያነሰ ሆኖ የተሰሩ መኖራቸው፣ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያን እንደሚጥስ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

21. ስለጉዳዩ በናሙና የታዩት መናኸሪያዎችን የሚስተዳድሩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ አገር ውስጥ በሚገጣጠሙትም ሆነ ለሌላ ዕቃ ማጓጓዣ ተሰርተው ወደ ህዝብ ማመላለሻነት በተቀየሩት ላይ በዋነኛነት የሚከሰት ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን በተደጋጋሚ ለማነጋገር ተሞክሮ ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

22. ይህንኑ በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ደረጃ ተሰጥቷቸው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ ካሉ 966 ተሽከርካሪዎች ውስጥ ከ 400 በላይ (41%) የሚሆኑት አዳዲስ ተሽከርካሪዎች መሆናቸውን እና ሁሉም ተሽከርካሪዎች ደረጃ ተሰጥቶቷቸው በየደረጃው አገልግሎት እየሰጡ እንደሚገኙ ሆኖም የህብረተሰቡ ፍላጎትና ያለው አቅርቦት አለመጣጣሙን ገልፀዋል፡፡ በደሰሳ ጥናቱ ላይ በተገለጹት ችግሮች እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ መስፈርትን በማያሟሉት ተሽከርካሪዎች ላይ የተወሰደውን የዕርምት ዕርምጃ በተመለከተ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

23. የተገልጋዩን አስተያየት ከግንዛቤ በማስገባት የዕርምት እርምጃ አለመውሰድ እና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት አለመተግበር ህብረተሰቡን ለከፋ ለእንግልትና ለአላስፈላጊ ወጪ ይዳርገዋል፡፡

**የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ቦታ መረጣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት መሆኑን በተመለከተ**

24. የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ግንባታዎችን በተመለከተ ባለስልጣን መ/ቤቱ ሚሟላት የሚገባቸውን መስፈርትና ደረጃ ሊያወጣ ይገባል፡፡ በአገሪቱ ያሉ የህዝብ

ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ መናኸሪያዎችም በወጣው መስፈርት መሰረት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት ሊሰጡና አዳዲሶችም በዚሁ መሰረት ሊገነቡ ይገባል፡፡

25. በትራንስፖርት ባለስልጣን ሥር የሚገኘው የድሬዳዋ መናኸሪያ ለጎርፍ ተጋላጭ በመሆኑ መናኸሪያው በክረምት ወራት ኃይለኛ ዝናብና ጎርፍ ሲኖር አገልግሎት መስጠት ስለሚያቆም ሳቢያን በተባለው አካባቢ አዲስ መናኸሪያ ለመገንባት ለእምነቱ እንደሻው የሥራ ተቋራጭ በብር 37, 804,687.00፣ ለአልቲሜት ፕላን ፒ.ኤል.ሲ. አማካሪ አርክቴክት መሐንዲስ አማካሪ ድርጅት በብር 624,312.00 በድምሩ ብር 38,428,999.00 በመቅጠር ሥራ ማስጀመሩ፣ ተቋራጭ ድርጅቱ በውሉ መሰረት መጋቢት 16 ቀን 2004 ዓ.ም ግንባታውን ጀምሮ በ18 ወራት ውስጥ አጠናቆ መስከረም 16 ቀን 2006 ዓ.ም እንደሚያስረክብ በውሉ ላይ ተቀምጧል፡፡ በዚህም መሰረት ለሥራ ተቋራጩ ቅድሚያ ክፍያ ብር 13,042,617.01 እና ለተሰሩ ሥራዎች ክፍያ ብር 2,603,670.12 በድምሩ ብር 15,646,287.12 የተከፈለና ለአማካሪ መሐንዲሱ በየወሩ ብር 34,684 ሂሳብ በኦዲቱ ወቅት የመስክ ጉብኝት እስከተደረገበት ሐምሌ 2005 ድረስ እየተከፈለ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት ለቢሮ አገልግሎት የሚሆነው ሕንፃ ግንባታ ከመጀመሩ በስተቀር የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች አገልግሎት የሚሰጡበት የማቆሚያሥፍራ ግንባታ ሥራ አለመጀመሩ ታውቋል፡፡



ፎቶ 1፡ መስከረም 2006 መጠናቀቅ የነበረበት የድሬዳዋ አዲሱ መናኸሪያ ግንባታ ያለበት ደረጃ

26. በአዲስ አበባ ከተማ በምስራቅ መውጫ በር ላምበረት አካባቢ እና በምዕራብ መውጫ በር

የአየር ጤና መናኸሪያዎቹ ግንባታቸው በ1995/96 በጀት ዓመት ቢጠናቀቀም ኦዲቱ እሰከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ስራ እንዳልጀመሩ ታውቋል፡፡ የአየር ጤና መናኸሪያ ወደ መናኸሪያው ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ከዋናው መንገድ የሚገነጠለው አስፋልት ጠባብ በመሆኑ ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ ተሽከርካሪዎችም ሆነ ተሣፋሪዎችን ለሚያመላልሱ የከተማ የትራንስፖርት አገልግሎት ለሚሰጡ የከተማ አውቶብስና ታክሲዎች ማቆሚያና ማራገፊያ ቦታዎች እንደሌለው ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. የሻሸመኔ እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች ግቢያቸው አስፋልት ያልተነጠፈና አሸዋ የፈሰሰበት ሲሆን በተለይ የቃሊት መናኸሪያ አሸዋው በአፈር የተዋጠ ወጣ ገባ በመሆኑ ለተሽከርካሪዎች ተዘጋጅቶ የነበረው ለመኪና ማቆሚያ የተሰራው ፉካ በአፈር የተዋጠ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

28. የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያዎቹ በ1969 ዓ.ም የተገነቡ በመሆኑ ባለሥልጣኑ ያወጣውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑን እና የአዲስ አበባው የአገር አቋራጭ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያ ከተሰራ ጀምሮ ጥገና ተደርጎለት እንደማያውቅ ለመረዳት ተችሏል፡፡

29. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ለአዲሱ መናኸሪያ ከከተማው መስተዳደር የተሰጣቸው ቦታ ቀድሞ የግብርና እንስሳት ህክምና ላብራቶሪ የነበረ በመሆኑና በወቅቱ ያላነሱት ንብረቶች ስለነበሩ ግንባታው ያልተጀመረ መሆኑን፣ የጊዜውን መጓተት በተመለከተ ግን ግንባታውን ክትትል እያደረገ የሚያሰራው ዋናው መ/ቤቱ መሆኑን፣ በውሉ መሰረት መናኸሪያው አለመጠናቀቁ ግን አገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ጫና እንደሚያሳድር እና ለተጨማሪ ወጪ እንደሚዳርጋቸው ገልጸዋል፡፡ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ የመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ መናኸሪያዎቹ መስፈርቱ ከመውጣቱ በፊት በ1969 ዓ.ም. የተገነቡ መሆኑን እና በየጊዜው ወቅታዊ ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

30. ይህንን በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የላምበረትና የአየር ጤና መናኸሪያዎችን የተረከቡት ቀድሞ አዲስ አበባ ትራንስፖርት ኮርፖሬሽን ከሚባል ሲሆን ውስጣቸው ያልተሟላና መንገዱ አመቺ ባለመሆኑ የኦፕሬሽን ሥራ ለመጀመር እንዳልቻሉ፣ ላምበረት ያለው ጣሪያው ማፍሰስ መጀመሩን፣ አጥሩም እየፈራረሰ መሆኑን፣ በቃሊቲ ያለው ጊዜያዊ መናኸሪያ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የባለሥልጣኑ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም መናኸሪያዎቹ ከተጠናቀቁ 10 ዓመት በመሆኑ ይህን ያህል ጊዜ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳወሰድ አገልግሎት ሳይሰጡ በመቀመጣቸው የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

31. ቀደም ብለው የተሰሩትም ሆነ አዲስ የተሰሩና በመሰራት ላይ ያሉ መናኸሪያዎች ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት እንዲያሟሉ ተደርጎ አገልግሎት እንዲሰጡ አለመደረጉ ህብረተሰቡ ጊዜና ወጪ ቆጣቢ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡

**የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች ለተጠቃሚዎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ሟሟላታቸውን በተመለከተ፣**

32. የህዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያዎች በውስጣቸው መሰረታዊ አገልግሎቶችን (የእሳት አደጋ ማጥፊያ፣ መጸዳጃዎች፣ መጠለያ፣ የካፍቴሪያ ክበብ ወዘተ...) በሚሟላት ተጠቃሚዎች ያለችግር አገልግሎቶችን ሊያገኙ ይገባል፡፡

33. በኦዲቱ ወቅት በናሙና የታዩት

- የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ የቃሊቲ እና የድሬዳዋ፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሀዋሳ ከተማ፣ በኦሮሚያ ክልል የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ግቢ ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ መሳሪያ የሌላቸው መሆኑን፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የቃሊቲ፣ የአስኮ እና የድሬዳዋ ከተማ፣ የሐዋሳ፣ የሻሸመኔ እና የአዳማ መናኸሪያዎች ለጠፉ ንብረቶች ማቆያ ቦታ የሌለ፣ የተሟላ የመፀዳጃ ቤቶች የሌላቸው መሆኑን፣
- የድሬዳዋ፣ የሐዋሳ እና የአዳማ መናኸሪያዎች የመንገደኞች ማረፊያና መጠበቂያ መጠለያ ቦታ ቢኖራቸውም መቀመጫ ወንበር የሌላቸው መሆኑን፣ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያዎች እና የሻሸመኔ መናኸሪያ ለተገልጋዮች የመጠለያ ቦታ የሌላቸው መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

34. የመናኸሪዎቹ ኃላፊዎቹ ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ መናኸሪዎቹ የተሰሩት ቀደም ብለው በመሆኑ በአሁን ወቅት በደረጃው ላይ ያለውን የማያሟሉ መሆኑን፣ መጸደጃዎቹ ደረጃቸውን ባይጠብቁም ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት ንጽህናቸውን ለመጠበቅ ጥረት እያደረጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

35. ለአገር አቋራጭ አውቶቢስ ተራ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ፣ የአስኮ መናኸሪያ እና የቃሊቲ ጊዜያዊ መናኸሪያ አስተዳደር ኃላፊዎች ከመናኸሪያው ፅዳት ጋር በተያያዘ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የመናኸሪያ ግቢዎቹ በፅዳት ሰራተኞች የሚፀዱ መሆኑን፣ የአውቶቢስ ተራ አገር አቋራጭ መናኸሪያ እና የቃሊቲ መናኸሪያ የመፀዳጃ ቤቶቹ በየጊዜው ሲሞሉ ቶሎ ስለማይመጠጡ የመናኸሪያውን ግቢ ፅዳት እንዳይጠበቅ እንደሚያደርገው፣ በተለይም በአገር አቋራጭ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ መፀዳጃ ቤቶች ሲሞሉ ፍሳሹ ወደ ውጪ ስለሚወጣ መናኸሪያውን የሚያበላሹበት ሁኔታ መኖሩን በቃሊቲ ደግሞ ለማስመጠጥ ወረፋ በመኖሩ ተገልጋዩ ሕብረተሰብ ሌላ የሚጠቀምበት ቦታ ባለመኖሩ በመናኸሪያ ግቢ አጥር ሥር እየተጠቀሙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

36. ይህንን በተመለከተ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የመናኸሪያ አስተዳደር ቡድን መሪዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት አውቶብስ መናኸሪያዎቹ መስፈርቱ ከመውጣቱ በፊት የተገነቡ መሆኑን፣ በየጊዜው ወቅታዊ ጥገና ያልተደረገላቸው መሆኑን ገልፀዋል፡፡ የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሳሪያ ለምን እንደሌላቸው ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡

37. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መናኸሪያዎች መሰረታዊ አገልግሎቶች አለሟሟላት ተጠቃሚዎችን ለእንግልት፣ ለበሽታና ለከፋ አደጋ ሊጥላቸው ይችላል፡፡

**የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ተግባራዊ መሆኑን በተመለከተ**

38. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ መናኸሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት መሆን አለበት፡፡ በዚህም መሰረት ስለአገልግሎት አሰጣጡ ለተሳፋሪዎች መረጃ የሚሰጥበት፣ ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች መግቢያና መውጫ ቦታዎች፣ ሸኚ በማይገባባት ቦታ የዕቃ መግፊያ ጋሪዎች እና የሚዛን አገልግሎት በሁሉም መናኸሪያዎች መሟላት አለባቸው፡፡

39. በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ አገር አቋራጭና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና ሻሸመኔ ከተማ ባሉ መናኸሪያዎች ውስጥ ተሳፋሪዎች ወደ መናኸሪያ ሲገቡ ስለአገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ የሌለ መሆኑ፣ የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ መናኸሪያ ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ ያለ ቢሆንም ለረጅም ዓመታት አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣ በሌሎች መናኸሪያዎች ውስጥ ቢል ቦርዱ የሌለ መሆኑ፣ በአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ ብቻ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ መግቢያ በር የተዘጋጀ ሲሆን፣ በሌሎቹ መናኸሪያዎች አለመዘጋጀቱ እና ሸኚ በማይገባባቸው መናኸሪያዎች ደንበኞች ዕቃቸውን ሊገፉበት የሚችሉ ጋሪዎች

እንደሌሉ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በአስኮና ቃሊቲ መናኸሪያ ግቢ ውስጥ መብራት ባለመኖሩ መንገደኞች ለስርቆት አደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ መኖሩና በቃሊቲ መናኸሪያ ውስጥ ለተገልጋዩ የሚዛን አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፣ እንዲሁም ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለያዩ አገልግሎቶች ወደሚሰጥባቸው ቦታዎች ለመንቀሳቀስ በሚመች መልኩ መናኸሪያዎቹ ያልተሰሩ መሆኑ ታውቋል፡፡

40. ስለጉዳዩ የአገር አቋራጭ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ አስተዳደር ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ለአቅመ ደካሞችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ መግቢያ በር የተዘጋጀ እና ትኬት ለመቁረጥ ቅድሚያ የሚሰጥ ሲሆን፣ የተለየ የመፀዳጃ ቤት አገልግሎት እና በግቢው ውስጥ የተለያዩ አገልግሎቶች እንዲያገኙ የተመቻቸ አለመሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከቃሊቲ መናኸሪያ አስተዳደር ጋር በተደረገው ቃለመጠይቅ በሰጡት ምላሽ መናኸሪያው ጊዜያዊ በመሆኑና መስፈርቱን አሟልቶ የተሰራ ባለመሆኑ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

41. ይህንንም ጉዳይ በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በባለስልጣኑ ስር ያሉ የአዲስ አበባ አገር አቋራጭ እና የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ መናኸሪያዎች የድሮ መናኸሪያዎች በመሆናቸው ችግሮቹ ሊታዩ መቻላቸውን፣ በመናኸሪያዎቹ የተወሰኑ ነገሮችን ለማስተካከል በጀት አስይዘው የባቡሩ ግንባታ ማለቅን እየተጠባበቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ቢሉም በተመለከትናቸው በባለስልጣኑ ስር ያሉ መናኸሪያዎች ከፍተኛ ወጪ የማይጠይቁ በመስፈርቱ መሰረት ሊሟሉ የሚገቡ ጉዳዮችን በመኖራቸው የተሰጠውን ምላሽ እንዳለ ለመቀበል ያዳግታል፡፡ ለተሳፋሪዎች በተለይም ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች አለመሟላታቸው ለእንግልትና አላስፈላጊ ወጪዎች እንዲዳረጉ ያደርጋል፡፡

**የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተሰጣቸው ስምሪትና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ፣**

42. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ባለንበረቶችና ማህበራት በተሰጣቸው ስምሪትና ለርቀቱ በተመደበው ታሪፍ መሰረት መስራት አለባቸው፡፡ የስምሪታቸውን መስመርና የዋጋ ታሪፍ በግልጽ በሚታይ ቦታ ሊለጥፉ ይገባል፡፡

43. በኦዲቱ ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ፣ የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ስምሪት የሚወስዱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መናኸሪያ ውስጥ

እያሉ የሚሄዱበትን መስመር እና የሚከፈለውን ዋጋ ታሪፍ አብዛኞቹ በውጭ በኩል ብቻ የሚለጥፉ ሲሆን ከመናኸሪያ ሲወጡ ግን በተለይ ሚኒባሶቹ የለጠፉትን ዋጋ አንሰተው የሚንቀሳቀሱ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

44. በአዲስ አበባ ከተማ፣ በሐዋሳ እና በሻሸመኔ የከተማ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ታክሲዎች የሚሄዱበትን መስመር የሚሳይ ሰሌዳ (ታፔላ) ተሰርቶላቸው የሚለጥፉ ቢሆንም ለርቀቱ የሚያስከፍሉትን ዋጋ የማይለጥፉ መሆኑን፣ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ለድጋፍ ሰጪነት በተጨማሪ የተመደቡት ኮድ 3 ሚኒባሶች የተመደቡበትን መስመርና የሚስከፍሉትን ዋጋ አብዛኛዎቹ የማይለጥፉ መሆኑን፣ ለህዝብ ማማላለሻ ፈቃድ ያልተሰጣቸው ደረጃ የሌላቸውና ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 ሰሌዳ የወሰዱ ሚኒባሶች ጭምር የታክሲ አገልግሎት የሚሰጡ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ የባለሥልጣኑ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የስምሪት መስመሮችን ርቀት እና የሚከፈለውን ዋጋ የሚያሳይ ሰሌዳ በከተማው የተለያየ ቦታ አሰርቶ ተክሎ የነበረ ቢሆንም ሰሌዳዎቹ ባልታወቀ ምክንያት መነሳታቸው በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

45. ከዚህ በተጨማሪ የአዲስ አበባ ከተማ የታክሲ ዞኒንግ ስምሪቱን በአግባቡ እንዲመሩ ኃላፊነት የተጣለባቸው የታክሲ ባለንብረት ማህበራት ቢሆኑም ከሥርዓቱ ውጭ በሚሰሩና እየቆራረጡ በሚጭኑ፣ ከታሪፍ በላይ በሚያስከፍሉ፣ ወደ ስምሪት ስርዓቱ በማይገቡ ታክሲዎች ላይ እርምጃ የማይወስዱ መሆኑን፣ በስራ መግቢያና መውጫ ሰዓት የታክሲዎች በሥራ ላይ አለመሰማራት፣ ከታሪፍ በላይ ማስከፈል፣ መስመር መቆራረጥ ችግሮች መኖሩን፣ በአዲስ አባባ በየተርሚናሉ የተደራጁ ተራ አስከባሪዎች ህግና ደንብ አክብረው አለመስራትና የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች እያቆራረጡ ሲጭኑም ሆነ ከታሪፍ በላይ ሲያስከፍሉ ያለመቆጣጠር፣ ችግሮች መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

46. ስለጉዳዩ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትራንስፖር ቢሮ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተገልጋዮችን ከታሪፍ በላይ አለማስከፈላቸው የእነርሱ ድርሻ መናኸሪያ ውስጥ ብቻ መሆኑንና ከመናኸሪያ ውጭ ያለውን በክልሉ አሰራር መሰረት የሚረጋገጠው በትራፊክ ፖሊሶች ብቻ መሆኑን፣ የስምሪት ሰራተኞች በወጣው መመሪያ መሰረት ከመናኸሪያ ውጭ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ እንዲሰሩ ስላልተፈቀደላቸው ቁጥጥሩ ውጤታማ ነው ለማለት እንደሚቸገሩ ገልጸዋል፡፡

47. የኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ኃላፊዎች ደግሞ በሰጡት ምላሽ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተገልጋዩን ከታሪፍ በላይ ማስከፈል እና ትርፍ ሰው ጭነው የመሄድ ችግሮች በመናኸሪያ ውስጥ በሚጭኑት ላይ እንደሌለ ነገር ግን ከመናኸሪያ ውጪ

በሚጭኑት ላይ ከታሪፍ በላይ የማስከፈል እና ትርፍ ሰውም የመጫን ችግሮች እንዳሉ፣ የትራንስፖርት ኤጀንሲው ተቆጣጣሪ ሰራተኞች ከትራፊክ ፖሊሶች ጋር የቁጥጥር ስራ እየሰሩ ቢገኙም ተቆጣጣሪዎቹ የጠራ አሰራር የሌላቸው መሆኑን፣ ህብረተሰቡም የትራንስፖርት እጥረት በመኖሩ ትርፍ ተጭኖ መሄድን እና ህገ ወጥ ታሪፍ መክፈልን የሚተባበር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች የሚሄዱትን መስመርና በርቀቱ የሚከፈለውን ዋጋ ለተሳፋሪው በሚታይ ቦታ አለመለጠፉን በተመለከተ በሰጡት ምላሽ፣ ይህ ችግር በግምገማም ላይ የታየ መሆኑን፣ የተቆጣጣሪው ግንዛቤም ሆነ ቁጥጥሩ አናሳ በመሆኑ ከትራፊኮች ጋር ውይይት ማድጋቸውን እና ተሳፋሪው ለከፈለው ገንዘብ ትኬት ያለመስጠት ችግርም በስፋት እንደሚታይ ገልጸዋል፡፡

48. የአዲስ አበባ ከተማ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ከአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች መረጃ ለመሰብሰብና ቃለመጠይቅ ለማቅረብ በተደጋጋሚ ሞክረን ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

49. የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ ባለንብረቶችና ማህበራት አገልግሎት የሚሰጡበትን መስመርና ታሪፍ በግልጽ በሚታይ ቦታ አለመለጠፋቸው እና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ቁጥጥሩን በአግባቡ አለማከናወናቸው ህብረተሰቡን ለተጨማሪ ወጪ እና ለአላስፈላጊ እንግልት እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡

**የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ምቹ መሆናቸውን በተመለከተ**

50. የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣...) ምቹ ሊሆኑ ይገባል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የክልል ፈቃድ ሰጪ አካላት ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ፈቃድ ሲሰጡ ይህ የተሟላ መሆኑንና በዚሁ መሰረት አገልግሎት መሰጠቱን ሊያረጋግጡ ይገባል፡፡

51. በኦዲቱ ወቅት በአዲስ አበባ አገር አቋራጭ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መለስተኛ፣ የአስኮ፣ የቃሊቲ ጊዜያዊ ፣የድሬዳዋ፣ የሀዋሳ፣ የአዳማ እና የሻሸመኔ ከተማ መናኸሪያዎች ውስጥ የተመለከትናቸው የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የተለየ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አመቺ መግቢያና መውጫ በር ያልተሰራላቸው መሆናቸው ታውቋል፡፡ የባለሥልጣኑ የድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መናኸሪያ ደግሞ አንድ በእጅ የሚገፋ ተንቀሳቃሽ መወጣጫ አሰረቶ ችግሩ ሲገጥም ወደ ተሽከርካሪው በማቅረብ አገልግሎት እንደሚሰጥ ታይቷል፡፡

52. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው መናኸሪያዎች ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ተሽከርካሪዎቹ ፈቃድ ሲሰጣቸው ይህን ሳያሟሉ በመሆኑ ችግሩ እንደተከሰተ፣ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን መንገደኞች በቤተሰቦቻቸው፣ በመናኸሪያው ሰራተኞችና በተሽከርካሪዎች ረዳት ድጋፍ እየተደረገላቸው እንደሚሳፈሩ ገልጸዋል፡፡

53. ይህን በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እየሰሩ ላሉት የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የሚሆን ተጣጣፊ የመወጣጫ ዲዛይን እየተሰራ በመሆኑ ሲጠናቀቅ ችግሩ እንደሚቀረፍ፣ ለወደፊቱ ግን ደረጃ አሰጣጥ ላይ እንደ አንድ መስፈርት ለማካተት መታሰቡን ገልጸዋል፡፡ የስራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ችግሩን ለመቅረፍ ተጣጣፊ መወጣጫ ዲዛይን ተሰርቶ ካለቀና ለተሽከርካሪዎች ብቃት ማረጋገጫ ዳሬክቶሬት ከተሰጠ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

54. የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከውጪ ተገዝተው ሲገቡም ሆነ እዚህ ተቀጥቅጠው ሲሰሩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣…) ታሳቢ በማድረግ አመቺ መግቢያና መውጫ በር እንዲኖራቸው ያልተደረገ በመሆኑ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን፣ ህፃናትና ሌሎች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወደ ተሽከርካሪ ለመግባትም ሆነ ለመውጣት ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ይገኛሉ፡፡

**ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለየደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን በተመለከተ፣**

55. የተለያየ ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ተገልጋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ እንዲለያቸው ለተሰጣቸው ደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

56. በባለስልጣን መ/ቤቱ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከደረጃ አንድ እስከ ሦስት ላሉት የተለያየ የመለያ ቀለም አዘጋጅቷል፡፡ በኦዲቱ ወቅት በተመለከትናቸው መናኸሪያዎች ውስጥ የሚገኙት የአገር አቋራጭ የህዝብ ማመላለሻዎች በሙሉ ለደረጃቸው የተሰጠውን መለያ ቀለም የተቀቡ ሲሆን፣ አንዳንድ መለስተኛ የህዝብ ማመላለሻ አውቶብሶች እና ሁሉም አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች (ሚኒባሶች) ለተሰጣቸው ደረጃ የሚገባውን ቀለም ተቀብተው አልተገኙም፡፡



ፎቶ. 2 ና 3 ለደረጃቸው የሚገባውን ቀለም ያልተቀቡ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድሬዳዋ መናኸሪያ እና ሻሸመኔ መናኸሪያ

57. ስለጉዳዩ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሁሉም ተሽከርካሪዎች መቀባት እንዳለባቸው ችግሩ የተፈጠረው ትኩረት ሰጥቶ ካለመስራት መሆኑን ሲገልጹ፣ የኦሮሚያ ክልል ኃላፊዎች ደግሞ ስለጉዳዩ መመሪያ እንደተላለፈና ከባለሀብቱም ጋር ውይይት እንደተደረገ፣ በ2006 በጀት ዓመት ሃምሳ ከመቶው (50%) የሚሆኑትን እንደሚቀቡ በእቅድ መያዙን፣ ቀለም ያልተቀቡትን ካልተቀባችሁ አትሰሩም ማለት አገልግሎቱ ላይ ተጽዕኖ ስለሚፈጥር እየታለፉ መሆኑን እና አዲስ ደረጃ የሚሰጣቸው ግን ካልተቀቡ ደረጃው እንደማይሰጣቸው ገልጸዋል፡፡

58. ይህንንም በተመለከተ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ከ44 መቀመጫ በታች ያላቸው ተሽከርካሪዎች ፍቃድ የሚያገኙት ከክልል መሆኑን፣ በአማራ ክልልም ይህንን ለማስከበር ከፍተኛ ስራ መሰራቱን እና ውጤት መገኘቱን ገልጸዋል፡፡

59. አንዳንድ መለስተኛና ሁሉም አነስተኛ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በየደረጃቸው ያለውን ቀለም ያልተቀቡ በመሆኑ ተገልጋዩ ህብረተሰብ በቀላሉ ደረጃቸውን እንዳይለዩና ለደረጃው የሚገባውን አገልግሎቶች እንዳያገኙ ከማድረጉም በላይ የህዝብ ማመላለሻ ፈቃድ የሌላቸው ተሽከርካሪዎች በህገወጥ መንገድ ሥምሪት ላይ እንዲሳተፉ በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

**የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች እና አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን አሟልተው አገልግሎት መስጠታቸውን በተመለከተ**

60. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ተሽከርካሪዎችም ሆነ አሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ማሟላት የሚገባቸውን ተጓዳኝ የሥራ መሳሪያዎችና ቁሶች አሟልተው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

61. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመለከትናቸው መናኸሪያዎች ውስጥ በአንዳንድ መለስተኛ እና አነስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት የሚሰጡ አሽከርካሪዎች እና ረዳቶች በመመሪው መሰረት ለደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) የማይለብሱ መሆኑን፣ ለምሳሌ በድሬዳዋ መናኸሪያ ውስጥ በናሙና ከታዩት አሥራ ስድስት አነስተኛና መለስተኛ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ውስጥ የሚሰሩ አሽከርካሪዎችም ሆኑ ረዳቶቹ ከአንዱ አሽከርካሪ በስተቀር ሌሎቹ መመሪያው ላይ የተገለፀው ቀለም ያለው ሸሚዝ፣ ሱሪም ሆነ ጃኬት ያልለበሱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

62. በሁሉም ደረጃ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎች አስገዳጅ ናቸው ተብሎ የተቀመጡ ቁሳቁሶችን፣ የመንገደኛ መቀመጫ ወንበር ከፊትና ከኋላው 730 ሚ.ሜ ስፋት፣ ጥራት ያለው ከጥጥ ጨርቆች የተሰራና በጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መጋረጃ፣ የተሽከርካሪው ወለል ሙሉ ለሙሉ "ባለሳንቲም" ኘላስቲክ የለበሰ መሆን እንዳለበት እነዚህ ካልተሟሉ ፈቃድ እንደማይሰጥ መመሪያው ይደነግጋል፡፡

63. በድሬዳዋ መናኸሪያ ውስጥ በናሙና ከታዩት 16 አነስተኛና መካከለኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ውስጥ ሁሉም የእሳት አደጋ መከላከያ መሣሪያ ያላቸው ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ የዘጠኙ (56%) ግን የመጠቀሚያው ጊዜቸው ያለፈ (አንዱ የመጠቀሚያው ጊዜ ከ10 ዓመት በላይ ያለፈው፣ ዘጠኙ ተሽከርካሪዎች (56%) ወዴት እንደሚሄዱ እና ምን ያህል ታሪፍ እንደሚያስከፍሉ የሚገልጽ ማስታወቂያ ያለጠፉ መሆኑን፣ ታሪፍ ያልለጠፉና የእሳት አደጋ ማጥፊያ መሣሪያው ጊዜ ያለፈባቸው ደግሞ 7 (44%) መሆናቸው፣ አስራ ሦስቱ መጋረጃቸው ከጥጥ ያልተሰራ፣ አንዱ ጭራሹን መጋረጃ የሌለው፣ አስራ ሁለቱ መስፈርቱን ያሟላ የወለል ንጣፍ የሌላቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ከዚህም በተጨማሪ ሥሪታቸው ለሌላ ተግባር የነበሩ ተሽከርካሪዎች ወደ ሕዝብ ማመላለሻነት እንዲቀየሩ ፈቃድ ሲሰጣቸው ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽካርካሪዎች ያወጣውን መስፈርት ሳያሟሉ ለታክሲ እና ከከተማ ውጭ እንዲያገለግሉ ሠሌዳና ደረጃ የሚሰጣቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

65. ስለጉዳዩ በትራንስፖርት ባለስልጣን የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን ደረጃና መመሪያ አሟልተው እየሰሩ ስለመሆኑ የድንገተኛ ምርመራ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊነቱን ለማረጋገጥ ከዋናው መ/ቤት በ2004 በተላከላቸው መመሪያ መሰረት ቅድመ ስምሪትና ድንገተኛ የቴክኒክ ምርመራ የተደረገ ሲሆን፣ በ2005 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ ትንሽ እንደሰሩ ባጋጠማቸው የባለሙያ እጥረት በእቅዱ የተያዘውን

ሙሉ ለሙሉ ሊሰሩ እንዳልቻሉ፣ ለሥምሪት ወደ መናኸሪያ ከሚመጡ ተሽከርካሪዎች ውስጥ የብቃት ማረጋገጫ በክልሎች ሲሰጥ ደረጃ 3 ሊሆን የሚገባውን ተሽከርካሪዎች ደረጃ 2 የማድረግ፣ ደረጃ 2 ሊሆን የሚገባውን ደረጃ 1 የማድረግ ችግሮች መኖራቸውን ገልፀዋል፡፡

66. ይህንንም በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ሳያሟሉ ከመናኸሪያ ፍቃድ እንደማይሰጣቸው፣ በእንዳንዱ ነገር ሙሉ ለሙሉ የጠራ ነው ማለት ባይቻልም በ7 ተቆጣጣሪዎች እየሰሩ እንደሚገኙ፣ በጊዜ ብዛት የሚታዩ ጉድለቶች እየተሟሉ እንደሚተገበር፣ ዋናው ነገር የለውጥ መንገድ መጀመሩ ትልቅ ስራ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ በአገር ውስጥ ከሌላ ተግባር ወደ ሕዝብ ማመላሻነት የሚቀየሩ ተሽከርካሪዎች በመስፈርቱ መሰረት መቀየራቸውን አረጋግጠው ፈቃድ መስጠት ስለሚገባቸው የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያዳግታል፡፡

67. የህዝብ ማመላለሻ ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት /ማህበራት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ብቃታቸውን በመለየት አስገዳጅ ናቸው ተብሎ የተቀመጠ መስፈርት ተግባራዊ በማድረግ ደረጃ አለመሰጠቱ ህብረተሰቡ ለሚከፍለው ገንዘብ ተመጣጣኝ አገልግሎት እንዳያገኝ ያደርገዋል፡፡

**የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን መኖሩን በተመለከተ**

68. ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባው የፍጥነት ወሰን ሊኖረው እና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

69. የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የካቲት 15/1961 ዓ.ም በደንብ ቁጥር 361/1961 የወጣ ቢሆንም 45 ዓመት የሆነው በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እና ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

70. ስለጉዳዩ በትራንስፖርት ባለሥልጣን ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ኃላፊዎች፣ ለድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ትራንስፖርት ቢሮ የግንዛቤ ትምህርት ዝግጅት ቡድን መሪ፣ ለሃረሪ ትራንስፖርት ጽ/ቤት ሃላፊ፣ ለደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትራንስፖር ቢሮ ምክትል ቢሮ ሃላፊ በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን አለመኖሩን፣ ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን የሚቆጣጠር መሣሪያ እንዲገጥሙም የሚያስገድድ ሥርዓት ባለመኖሩ ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑን እና የፍጥነት ወሰን መመሪያ በአገር አቀፍ ደረጃ መውጣቱን እየተጠባበቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

71. ይህንኑ በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የፍጥነት ወሰን ለመተግበር ከባለድርሻ አካለት ጋር ከተወያዩ በኋላ በ2006 ዓ.ም ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

72. የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ሊሄድበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን የሚደነግግ መመሪያ በ1961 ዓ.ም የወጣ ሲሆን፣መመሪያው የቆየና በአሁኑ ሰዓት ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ ወቅታዊ መሻሻል ያልተደረገበት በመሆኑ የሕዝብ ማመላለሻ አሽከርካሪዎች በከፍተኛ ፍጥነት እየተጓዙ ከፍተኛ የሆነ የሕይወት መጥፋትናና የንብረት ውድመትን እያስከተለ ይገኛል፡፡



ፎቶ 4: ከጅግጅጋና ከሐረር የሚመጡ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መካከል የደረሰ አደጋ



ፎቶ 5፡ ከድሬዳዋናና ከደንገጎ መካከል የደረሰ አደጋ

## 2.2 ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው እያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

**ባለስልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ሥምሪትን ለመግታት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን  በተመለከተ**

73. ባለስልጣን መ/ቤቱ በየቀኑ የሚፈፀሙ ሕገወጥ ስምሪትንና የሌሊት ጉዞን ለማስቆም የሚረዱ የአሰራር ሥርዓቶች ሊዘረጋና ሥርዓቱን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች  በክልሎችና በባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡

74. ባለስልጣን መ/ቤቱ የካቲት 2005 ዓ.ም ሕገ ወጥ ስምሪትንና የሌሊት ጉዞ ለመግታት የሚያስችል አገራዊ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎች አውጥቶ ለቅርንጫፍ መ/ቤቶችና ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ማሰራጨቱ ታውቋል፡፡ ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ባየናቸው መናኸሪዎያችም ሆነ በናሙና በተመረጡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የትራንስፖር ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ ምእራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ትንስፖርት ኤጀንሲ፣ በአዳማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት እና በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮዎች መረዳት እንደተቻለው የሕገ ወጥ ሥምሪቱ በየመናኸሪያዎች በር ላይ ጭምር በግልፅ የሚከናወን መሆኑ፣ ድርጊቱን ለመከላከል በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ወጥ የሆነና ቅንጅታዊ አሰራር የሌለ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

75. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ተጠይቀው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል  የትራንስፖር ቢሮ ኃላፊዎች አነስተኛና መለስተኛ ተሽከርካሪዎች ከመናኸሪያ ውጪ በሆቴል ቤትና ጋራጅ በመጫን የስምሪት መውጫ ከመናኸሪያ የተሰጣቸው በማስመሰል የመሰማራት ሁኔታ መኖሩን፣  ችግሩን ለመቅረፍ ከአጎራባች ከተሞች ጋር የተቀናጀ ቁጥጥር እያደረጉ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ቆሟል ማለት የማይቻል መሆኑን ገልፀዋል

76. በኦሮሚያ ክልል የምእራብ አርሲ ዞን ሻሸመኔ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ኤጀንሲ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የስራ ሂደት መሪ ጋር በተደረገው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ የሌሊት ህገ ወጥ ስምሪት እንደሚበዛና  የሌሊት ጉዞ  ለማስቆም የወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች ብዙም ስራ ላይ እንዳልዋሉ ገልፀዋል፡፡

77. በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ሃላፊና የትራንስፖርት አገልግሎት እና

አቅርቦት ስራ ሂደት ባለቤት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ መነሻቸውን ከተለያየ ክልል ያደረጉ ተሽከርካሪዎች ክልላቸው ሲገቡ ተቆጣጥረው ከ150 ኪ.ሜ በላይ እና ሌሊት በሚጓዙ ህገወጦች ላይ እርምጃ እንደሚወስዱ፣ በአሁኑ ወቅት ሌሊት ላይ የሚቆጣጠርላቸው ተቆጣጣሪ የሌለ መሆኑን እና የሚቆጣጠሩት የትራፊክ ፖሊሶች ብቻ መሆናቸው እና ትራፊክም የፀዳ አሰራር እየሰራ ነው ለማለት የማያስደፍር መሆኑን፣ በአዲስ አበባ ብቻ 192 በህገወጥ መንገድ የሚጭኑባቸው ቦታዎች እንዳሉ መጠናቱን እና ህገወጦችን ከመነሻቸው ቁጥጥር ቢደረግ የተሻለ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝም ክልል ተሻጋሪ የለሊት ጉዞ ማለትም ከተለያዩ አቅጣጫዎች ከሀረር ፣ ከጅጅጋ ፣ ከባህርዳር፣ ከመቀሌና ከደሴ ኦሮሚያ ክልልን አቋርጠው ወደ አዲስ አበባ እየመጡ ቢሆንም የትራንስፖርት ባለስልጣን ክልሎችን አስተባብሮ በመስራት ለማስቆም የሚያደረገው ጥረት አናሳ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

78. ይህንኑ በተመለከተ የባለስልጣን መ/ቤቱ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በ2006 ዓ. ም ድርጊቱን ለመከላከል የጋራ ውይይት መደረጉንና ቃለጉባኤም የተያዘ መሆኑን፣ ክልሎች የራሳቸው ስልጣን ስላላቸው በክልላቸው ያለውን የመቆጣጠር ስራ መስራት እንዳለባቸው፣ በአሁኑ ወቅት ካለው አሳሳቢነት አንፃር ኮሚቴም ተሰይሞ ለመንገድ ደህንነት ዳይሬክቶሬት ተሠጥቶ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን እየሰሩ እንደሆነ፣ ከመናኸሪያ ውጪ ከትራፊክ ፖሊስ ጋር በጋራ የቁጥጥር ስራው እየተሰራ እንደሚገኝ፣ በየወሩ አንዴ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሁለቴና ከዛ በላይ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በሌሎች ዘርፎች እንደሚነጋገሩ ገልፀዋል፡፡

79. የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም በናሙና የታዩ የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች እንደገለፁት የሚደረገው የጋራ የውይይት መድረክ በአሁን ጊዜ ብዙም እንቅስቃሴ እንደሌለውና እንደተቋረጠ ገልፀዋል፡፡

80. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር ተቀናጅቶ የቀንም ሆነ የሌሊት ህገወጥ ስምሪት ላይ የተጠናቀረ ቁጥጥር በመዘርጋት ተግባራዊ አለማድረጉ ህግ አስከባሪዎችን ለመሸሽ በሚደረገው ጥረት የሰዎች ህይወት አደጋ ላይ እንዲወድቁ ከማድረጉም በላይ ለህገወጥ የሰዎች ዝውውርና ንግድ የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

**ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ የሚያደርገውን ክትትል በተመለከተ**

81. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች

ላይ ክትትል በማድረግ ወጥ የሆነና አስተማሪ ሊሆን የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

82. መጋቢት 2005 ዓ.ም በተሻሻለው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫና ሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት የተሽከርካሪ የኋላ ሰሌዳ በሚመለከተው አካል ከተፈታ በኋላ ቅጣቱን ሳይፈፅም በያዘው የቅጣት ሰነድ (የቁጥጥር ክስ ወረቀት) መስራት እንደማይፈቀድለት፣ ይህንን ህግ ጥሶ የተገኘ አሽከርካሪ ላይ ብር 4000 ቅጣት እና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ መሰረዝ እንደሚያደርስ መመሪያው ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፣ በመስክ ጉብኝት ወቅት በርካታ ቁጥር ያላቸው ሚኒባሶች የኋላ ታርጋቸው ተነቅሎ የስምሪት ፍቃድ ተሰጥቷቸው ሲንቀሳቀሱ ታይቷል፡፡



ፎቶ 6ና 7 የኋላ ሰሌዳቸው ተፈቶ የህዝብ ማመላለሻ አገልግሎት እየሰጡ የነበሩ (ከሻሸመኔ- ሀዋሳ፣ ሞጆ ከተማ)

83. በኦዲቱ ወቅት በታዩት በአዲስ አበባ፣ በድሬዳዋ፣ በሐዋሳ፣ በሻሸመኔ እና በአዳማ በሚገኙ መናኸሪያዎች እና ከእነዚህ መናኸሪያዎች ስምሪት በሚሰጣቸው መስመሮች ላይ የኋላ ሰሌዳቸው የተፈቱ ሚኒባሶችና አውቶብሶች መኖራቸው ታውቋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማም ታክሲዎችና በድጋፍ ሰጪነት የተሰማሩ ኮድ ሶስት ሚኒባሶች የኋላ ሰሌዳቸው ተፈትተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

84. በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ኃላፊዎች አንዳንድ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የኋላ ሰሌዳቸው ተፈቶ የትራንስፖርት አገልግሎት ለምን እንደሚሰጡ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ የሚፈታው የፊት ሰሌዳ እንደሆነ ነገር ግን የፊት ሰሌዳቸው እንዳይፈታ የሚበይዱ እንደአሉ፣ ለቁጥጥር እንዳይመች የኋላ ሰሌዳቸውንም ሆነ የፊት ሰሌዳቸውን አውልቀው ፈተው የሚይዙበት ሁኔታ መኖሩን፣ የፊት ሰሌዳ ሲፈታባቸው የኋላውን ፈተው ወደ ፊት የማድረግም ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

85. ስለጉዳዩ የሚመለከታቸው የመናኸሪያና የትራንስፖርት ጽ/ቤት ኃላፊዎች ተጠይቀው ሰሌዳን በዋነኛነት የሚፈቱት የትራፊክ ፖሊሶች ሲሆኑ አሽከርካሪዎች ተሳፋሪዎችን አራግፈውና ቅጣቱን ከፍለው እስኪመለሱ ድረስ የተወሰነ ጊዜ ስለሚሰጣቸው ስምሪት እንደማይከለክሉ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ሰሌዳ መፈታት ካለበት የሚፈታው የፊት ለፊቱ እንጂ የኋላ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ አልተቀበልነውም፡፡

86. በአዲስ አበባ ከተማ ስላለው የህገ ወጥ ትራንስፖርት አገልግሎትና የኋላ ሰሌዳቸው የተፈታ ታክሲዎችና ድጋፍ ሰጪ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን በፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎችን ለማነጋገር ተሞክሮ ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

87. የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የኋላ ሰሌዳቸው ተፈቶ በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ ለቁጥጥር አዳጋች ከመሆኑም በላይ ለህገወጥ የሰዎች ዝውውርና ለኮንትሮባንድ ንግድ በር ይከፍታል፡፡

## 2.3 ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀልጣፋ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የዘረጋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ

**ባለስልጣን መ/ቤቱ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርዓት የዘረጋና በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን በተመለከተ**

88. ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

89. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የራሱንም ሆነ ከስሩ ያሉ መናኸሪያዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እንዲሁም የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ያልተደገፈ መሆኑን ወቅታዊና አገራዊ የትራንስፖርት መረጃ በተሟላ መልኩ ያልተያዘ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

90. ስለጉዳዩ የባለስልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በመረጃ ስርጭትና ክምችት የተጀመሩ ጥረቶች ቢኖሩም የተሳካ ስራ አለመሰራቱን ገልፀዋል፡፡

91. ባለስልጣን መ/ቤቱ በትራንስፖርት መረጃ አያያዝ ላይ የሚሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑና አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ

ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ያለማድረጉ በወቅታዊ መረጃ ላይ የተደገፈ ውሳኔ ለመወሰን አዳጋች ያደርገዋል፡፡

**በባለስልጣን መ/ቤቱ በሚወጡ አገራዊ ደንቦች መመሪያዎችና መስፈርቶች ላይ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትን የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠቱን በተመለከተ**

92. ባለስልጣን መ/ቤቱ የባለድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለማሳደግ በሚወጡ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶችና መስፈርቶች የተለያዩ ጥናቶች የስራ እቅዶች የመሳሰሉት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥና ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል፡፡

93. በናሙና ከተመረጡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የትራንስፖርት ቢሮ፣ በኦሮሚያ ክልል የክልሉ ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ጽ/ቤት፣ ምዕራብ አርሲ ዞን የሻሸመኔ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ፣ በሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮ የሥራ ኃላፊዎች ባለሥልጣን መ/ቤቱ በህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ በየጊዜው በሚወጡ አገራዊ ስታንዳርዶች ላይ ለሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ተከታታይነት ባለው መልኩ የማይሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

94. በትራንስፖርት ባለስልጣን የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የትራንስፖርት አገልግሎት እና አቅርቦት ስምሪት የሥራ ሂደት መሪ ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በትራንስፖርት ፍሰት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች በየመስመሩ ያሉ ተቆጣጣሪዎች በዘርፉ ያላቸው ግንዛቤ አናሳነት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

95. የሐረሪ ክልላዊ መንግስት ትራንስፖርት ቢሮ በተላከላቸው መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከትራንስፖርት ባለስልጣን ምንም አይነት ስልጠና ተሰጥቷቸው እንደማያውቅ ገልፀዋል፡፡ በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ ምክትል ኃላፊና የትራንስፖርት አገልግሎት እና አቅርቦት ስራ ሂደት ባለቤት በሰጡት ምላሽ አዳዲስ መመሪያዎች ሲወጡ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጡ ሆኖም በፌደራል ደረጃ የትራንስፖርት ዘርፉን በተመለከተ የጋራ መድረክ የሚፈጠርበት ሁኔታ ቢመቻች ጥሩ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

96. ስለጉዳዩ የባለሥልጣኑ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ደንቦች መመሪያዎችና መስፈርቶች በውይይት ካዳበሩ በኋላ ተዘጋጅተው ለሁሉም ክልሎች እንዲደርስ እንደሚደረግ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ እንደሚሰጥ ሆኖም በክልል የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በየጊዜው ስለሚቀያየሩ ክፍተቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ገልፀዋል፡፡

97. በየጊዜው የሚወጡ አገር አቀፍ መመሪዎችና መስፈርቶች ላይ በቂ ግንዛቤ አለመሰጠቱ በአገር አቀፊወ ደረጃ ወጥ የሆነ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

**የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ማቋቋሙን በተመለከተ፣**

98. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ከተሞች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከፍቶ ለፌደራል መንግስት ተጠሪ የሆኑ ከተሞች የትራንስፖርት አገልግሎቱ እንዲስፋፋ ማድረግ አለበት፡፡

99. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በድሬዳዋ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የከፈተ ሲሆን የአዲስ አበባውን በቁጥር ትባ/ዋዳ/287/11/02 ቀን 15/11/02 በተፃፈ ደብዳቤ ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ውክልና መስጠቱ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሰጠው ውክልና መሰረት መሰራቱን የማይከታተል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውክልናውን ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ለባለሥልጣኑ የሥራ አፈጻጸሙን ሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አቅርቦ የማያውቅና የቅርንጫፉ ሂሳብ በባለሥልጣኑ አመታዊ ሂሳብ መግለጫ ላይ የማይካተት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

100. ይህንን በተመለከተ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍን ወክሎ ከሚሰራው የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ባለስልጣን በኦዲቱ ወቅት መረጃ ለመሰብሰብ በተዳጋሚ ተሞክሮ መረጃ ለመስጠትም ሆነ መጠይቅ ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነው አልተገኙም፡፡

101. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሰጠው ውክልና መሰረት በአግባቡ እየተሰራ መሆኑን አለመከታተሉ በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት እየተወጣ መሆኑን ለማረጋገጥ አዳጋች ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

102. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እንቅፋት የሆኑ የአሠራር ድክመቶችና ግድፈቶች ያሉበት መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተገንዝበናል፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

103. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው እያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

- የመናኸሪያዎች አደረጃጀት፣ አሠራር እና አገልግሎት አሠጣጥ ከቦታ ቦታ የተለያየ በመሆኑ ተገልጋዩ ሥርዓት ያለው እና ወጥ የሆነ ተጠቃሚውን የሚያረካ ምቹና ደህንነቱ የተረጋገጠ የመናኸሪያ አገልግሎት እያገኘ አለመሆኑ፣
- የተሳፋሪዎች የአገልግሎት ፍላጎቶች ላይ በሚደረጉ ጥናቶች መሠረት እርምጃ የማይወሰድ መሆኑ፣
- ከተፈቀደላቸው የወንበር ቁጥር በላይ ጨምረው ተሳፋሪ የሚጭኑ መለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣
- ለሌላ ተግባር የተሰሩ ተሽከርካሪዎች የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ ተደርገው ሲቀየሩ ባለሥልጠኑ ያወጣውን መሰፍርት በሚያሟላ መልኩ አለመሆኑ፣
- የድሬዳዋ አዲስ መናኸሪያ ግንባታ የዘገየ መሆኑ፣
- ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ይውላል ተብሎ የተገነባው የአየር ጤና መናኸሪያ ለተሽከርካሪዎች መግቢያና መውጫ አመቺ አለመሆኑ፣
- የአዲስ አበባ የአገር አቋራጭ አውቶቢስ ተራ መናኸሪያ፣ የአዲስ ከተማ አነስተኛና መካከለኛ የሕዝብ ትራንስፖርት መናኸሪያ፣ የቃሊቲ (ጊዜያዊ) መናኸሪያ፣ የድሬዳዋ መናኸሪያ እና የሐረሪ መናኸሪያ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት የማያሟሉ መሆኑን፣
- በተወሰነ የጊዜ ገደብ ወቅታዊ ጥገና ለሚያስፈልጋቸው መናኸሪያዎች ጥገና የማይደረግላቸው መሆኑ ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ የላምበረትና የአየር ጤና መናኸሪያዎች ግንባታቸው

ከተጠናቀቀ ከአስር ዓመት በላይ ቢሆነውም ርክክብ ተደርጎ ስራ ያልጀመሩ መሆኑ፣

- ተሳፋሪዎች ወደ መናኸሪያ ሲገቡ ስለአገልግሎት አሰጣጡ መረጃ የሚያገኙበት ሁኔታ አለመኖር እና ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ በመናኸሪያዎች ውስጥ አለመኖር፣
- በመናኸሪያ ግቢ ውስጥ መብራትና ውሃ፣ የእንግዳ ማረፊያዎች እና መፀዳጃ ቤቶች የተሟላ አለመሆንና ደረጃቸውን በጠበቀ መልኩ አገልግሎት የሚሰጡ አለመሆኑ፣
- የመናኸሪያዎቹ ግንባታ ለአካል ጉዳተኞችና አቅመ ደካሞች ወደ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ለመግባትና ለመውጣት አመቺ አለመሆን፣
- የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ ባለንብረቶችና ማህበራት የሚሰማሩበትን መስመርና ታሪፉን በግልጽ በሚታይ ቦታ አለመለጠፋቸውና መስመር እየቆራረጡ የሚሰሩ መሆኑን፣
- በአገር አቀፍ ደረጃ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ከውጪ ሲገቡም ሆነ አገር ውስጥ ተቀጥቅጠው ሲሰሩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች (አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣...) በቀላሉ ለመሳፈርም ሆነ ለመወረድ እንዲመቹ ተደርገው ያልተሰሩ መሆኑ፣
- ሁሉም አነስተኛ እና አንዳንድ መለስተኛ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በየደረጃቸው የተመደበውን ቀለም ያልተቀቡ መሆኑ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ብቃት በመለየት  አስገዳጅ ናቸው ተብሎ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት ሳያሟሉ ስምሪት የሚሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች መኖር፣
- በ1961 ዓ.ም. የወጣው የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች ሊሄድበት የሚገባ የፍጥነት ወሰን መመሪያ ኦዲቱ እሰከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መሻሻል ያልተደረገበት መሆኑ፣

104. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው ያደረገ መሆኑን  በተመለከተ፣

- የቀንም ሆነ የሌሊት ህገወጥ ስምሪት ላይ ዘላቂነት ያለው ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑ፣

- ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥራ ፈቃድና ደረጃ ያልተሰጣቸው ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 ሰሌዳ የተሰጣቸው አነስተኛ ተሸከርካሪዎች (ሚኒባሶች) በከተማ ውስጥም ሆነ ከከተማ ውጭ በህገወጥ መንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት እየሰጡ መሆኑ፣
- የኋላ ሠሌዳቸው ተፈትቶ የስምሪት አገልግሎት የሚሰጡ የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች መኖራቸው፣

105. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀልጣፋ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የተደራጀ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝ ሥርዓት ያልዘረጋ መሆኑ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ልውውጥ ስርአት የሌለው መሆኑ፣
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚወጡ አገራዊ ስታንዳርዶች ላይ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮም ሆነ ለባለድርሻ አካላት በተጠናከረ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍን ጽ/ቤት ሥራውን በውክልና እንዲሰራ የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር (የከተማው መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ) ውክልና ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ለባለሥልጣኑ የሥራ አፈጻጸም ሆነ የፋይናንስ ሪፖርት አቅርቦ የማያውቅ መሆኑ፣

ናቸው፡፡

106. በአጠቃላይ የትራንስፖርት ባለሥልጣን መ/ቤት የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን ካላደረገ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት ካልዘረጋ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት የሚሰራው ሥራ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙቱን ግድፈቶችና ድክመቶች ለማሻሻል ይረዳሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሃሳቦች

107. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራው እያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

- ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እና ከክልሎች ጋር በመተባበር የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡን ተደራሽ፣ ደህንነቱን ጥራቱንና ምቹቱን የጠበቀ ለማድረግ የሚያስችለውን የአሰራር ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውል መናኸሪያ ቦታ መረጣ እና ግንባታ ሲደረግ ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን መስፈርት ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥና ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ በሥራ ላይ ያሉ መናኸሪያችም መስፈርቱን አሟልተው አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ አለበት፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የድሬዳዋ መናኸሪያ ግንባታ በፍጥነት እንዲጠናቀቅ አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይኖርበታል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥና ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪዎች በተሰጣቸው ስምሪትና ታሪፍ መሰረት አገልግሎት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአየርጤና አካባቢ የተሰራው መናኸሪያ ለሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሚያመች መልኩ መንገዱ ተስተካክሎ ወደ ሥራ እንዲገባ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻዎች ከውጪ ሲገቡም ሆነ አገር ውስጥ ተቀጥቅጠው ሲሰሩ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ታሳቢ ያደረጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ አሁን በሥራ ላይ ያሉትን አመቺ ለማድረግ የተዘጋጀው ዲዛይን በፍጥነት ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ አለበት፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው የሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ደረጃ የተሰጣቸው መለስተኛና አነስተኛ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በሙሉ ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን የሚያረጋግጥበትን የአሠራር

ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግና ይህን ተግባራዊ ባላደረጉ ላይ እርምጃ መውሰድ ይገባዋል፡፡

- ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ብቃት በመለየት አስገዳጅ ናቸው ተብሎ በየደረጃው የተቀመጠውን መስፈርት አሟልተው በየደረጃቸው መስራታቸውን አሽከርካሪዎቹም ሆኑ ረዳቶች በወጣው መስፈርት መሰረት ለደረጃው የሚገባውን የደንብ ልብስ መልበሳቸውን ሊያረጋግጥ ይገባዋል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ከ45 ዓመት በፊት የወጣውን የፍጥነት ወሰን መመሪያ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመመካከር ወቅታዊ ማድረግ እና በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተልና ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

108. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን በተመለከተ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ በቀን እና በሌሊት የሚፈፀሙ ሕገወጥ ስምሪትን ለማስቆም የወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች በአገር አቀፍ ደረጃ በሁሉም ክልሎችና የባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር እንዲሁም ሁሉንም ክልሎች በማስተባበር ወጥና ቀጣይነት ያለው ቅንጅታዊ የአሠራር ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ያወጣውን የስምሪት አፈፃፀም መመሪያ በሁሉም ክልሎች ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚመለከተው አካል የኋላ ሰሌዳቸው የተፈቱ ተሽከርካሪዎች ከመናኸሪያ የስምሪት ፈቃድ እንዳይሰጣቸው፣ ሰሌዳቸው ተፈቶ በመንገድ ላይ እንዳይንቀሳቀሱ የሚያደርግበትን እና እርምጃ የሚወሰድበትን የአሰራር ስርዓት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የሕዝብ ማመላለሻ ፈቃድ የተሰጣቸው ደረጃቸውና የማህበራቸው ዓርማ ለተመልካች በሚታይና በተወሰነ ሥፍራ ብቻ የሚለጥፉበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሕገወጥ የትራንስፖርት ስምሪትን ለመከላከል በባለሥልጣኑም ሆነ በክልሎች ለሌላ ንግድ ሥራ ኮድ 3 የሚሰጣቸው ሚኒባሶች ፈቃድ የጠየቁበትን የንግድ ድርጅት ዓርማ የሚገልጽ

ለተቆጣጣሪዎችም ሆነ ለሌላው በሚታይ ሥፍራ ላይ የሚለጥፉበትን የአሰራር ሥርዓት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ አለበት፡፡

109. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ቀልጣፋ አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ፣

- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለትራንስፖርት መረጃ አያያዝ የሚሰጠው ትኩረት በማሳደግና አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ስርአት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ በማድረግ አስተማማኝ ጥራት ያለውና ወቅታዊ መረጃ በተሟላ መልኩ ሊይዝ ይገባል፡፡
- በባለሥልጣን መ/ቤቱ በወጡ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶች፣ ስታንዳርዶች ፣ የተለያዩ ጥናቶች ፣ የስራ እቅዶች የመሳሰሉትን ላይ ለክልል ትራንስፖርት ቢሮዎችም ሆነ ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥና ተግባራዊ መደረጉን ሊከታተል ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተሰጠው ውክልና መሰረት መስራቱን እና በየጊዜው የስራ አፈጻጸም እና የፋይናንስ ሪፖርቶች ማቅርቡን ሊከታተልና ሊቆጣጠር ይገባል፡፡

110. በአጠቃላይ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ፍትሃዊና የተጠቃሚውን የመክፈል አቅም ያገናዘበ እንዲሆን በማድረግ የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው ያሉበትን የአሰራር ክፍተቶችና ድክመቶች ማሻሻልና ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

111. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት፣ በኦዲቱ የታየው የባለሥልጣን መ/ቤቱ ቅ/ጽ/ቤት እና የክልል ትራንስፖርት ቢሮዎች ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

# አባሪ 1 የትራንስፖርት ባለሥልጣን ድርጅታዊ መዋቅር

**የትራንስፖርት ሚኒስቴር**

**የትራንስፖርት ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር**

**የትራንስፖርት አመራርና የትራፊክ ደህንነት እንስቲትዩት**

**የኦዲት ስራ ሂደት**

**ድጋፍ ሰጪ ዳይሬክቶሬት**

- የሰው ሃብት ሥራ አመራርና ልማት ስራ ሂደት
- የፋይናንስ ግዢና ንብረት አስተዳደር
- የማስታወቂያና ህዝብ ግንኙነት ስራ ሂደት
- የህግ አገልግሎት ስራ ሂደት
- የሪፎርም መከታተያ ፅ/ቤት
- የስነ ምግባርና ቅሬታ መከታተያ የስራ ሂደት
- የሰሌዳና ምልክቶች ምርትና ስርጭት የስራ ሂደት
- የተሽከርካሪ ስምሪት፣ ጥገና እና ጠቅላላ አገልግሎት የስራ ሂደት

**የተሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት**

- የተሽከርካሪ ብቃት ክትትልና ቁጥጥር ቡድን
- የተሽከርካሪ ተቋማት ብቃት ጥናት ቡድን

**የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት**

- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገጫ ክትትልና ቁጥጥር ቡድን
- የአሽከርካሪ ብቃት ማረጋገቻ ጥናት ቡድን
- የትራንስፖርት ቴክኒሻን ብቃት ማረጋገጫ ቡድን
  የፌደራል መ/ፈ ዕድሳት ቡድን

**የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት**

- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ሲስተን ጥናት ቡድን
- የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ግንዛቤና ትምህርት/ዝግጅት ቡድን
- የመንገድ ክትትል ቡድን

**የትራንስፖርት መረጃ አሰባሰብና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት**

- የዳታ በቤዝ አስተዳደርና መረጃ ስርጭት ቡድን
- የመረጃ መረብ አስተዳደርና ደህንነት ቡድን
- የሲስተም ሶፈት ዌርና ልማት ቡድን

**የጭነት ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት**

- የአደረጃጀት ብቃት ማረጋገጫ ቡድን
- የጭነት ትራንስፖርት ሎጂስቲክ ክትትልና ድጋፍ ቡድን
- የአቅም ግንባታ ድጋፍ ቡድን
- የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ድንበር ተሸገር ፍቃድ መስጫ ቡድን

**የህዝብ ትራንስፖርት ብቃት ማረጋገጫ ዳይሬክቶሬት**

- የአደጃጀትና ብቃት ማረጋገጫ ቡድን
- የአቅም ግንባታና ጥናት ቡድን
- የስምሪት ፣ ክትትልና መናኸሪያ አስተዳደር ቡድኖች(6)

**የትራንስፖርት ፖሊሲ ጥናትና ፕላን ዳይሬክቶሬት**

- የዕቅድና ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ቡድን
- የትራንስፖርት ፖሊሲ ጥናትና ምርምር ቡድን

**የአዲስ አበባ ትራንስፖርት ቅ/መ/ቤት**

**የድሬዳዋ ትራንስፖርት ቅ/መ/ቤት**

# አባሪ ሁለት፡- ኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት ጭብጥ | ተ.ቁ | የኦዲት መመዘኛ መስፈርት |
|---|---|---|
| 1. ባለሥልጣን መ/ቤቱ የደንበኞችን አገልግሎት እርካታ በተመለከተ ደህንነቱ የተረጋገጠ፣ ቀልጣፋ፣ የተሟላ እና የተመጣጠነ የትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ስርአት የዘጋና ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ | 1 | የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ያለው የደንበኞችን ፍላጎት የሚያረካ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በጊዜ፣ ምቾት፣ አቅርቦትና በዋጋ ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 2 | የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ቦታ መረጣ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ |
| | 3 | ባለስልጣን መ/ቤቱም ሆነ የክልል ትራንስፖርት ባለስልጣን የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የከተማ ማስተር ፕላን በሚዘጋጅበት ጊዜ ተሳትፎ በማድረግ ለመናኸሪያ የሚውሉ ቦታዎች በአግባቡ በማስተር ፕላኑ መካተቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 4 | የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ ግንባታ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ ሊገነባ ይገባል፡፡ |
| | 5 | የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አስተዳደር ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 6 | የህዝብ ትራንስፖርት የመናኸሪያ አገልግሎት አሰጣጥ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባወጣው መስፈርት መሰረት ተግባራዊ መሆኑን ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 7 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ከክልልም ሆነ በፌዴራል ደረጃ ሕጋዊ ስምሪት ተሰጥቷቸው የተሰማሩ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች በየትኛውም ክልል ወይም የፌዴራል መናኸሪያ ሕጋዊ፣ አግባብነትና ተቀባይነት ኖሯቸው መስራታቸውን ሊከታተል ይገባል |
| | 8 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የተገልጋዩን አቅም ያገናዘበና የተሸከርካሪ ባለንብረቶችን በማይጎዳ መልኩ ተመጣጣኝ የዋጋ ተመን ( ታሪፍ) ሊያወጣ ይገባል፡፡ |
| | 9 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ለሚሰጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ተገልጋዮችን በወጣው ታሪፍ መሰረት ማስከፈላቸውን የሚያረጋግጥበት ስርዓት ዘርግቶ ተግባራዊነቱን ሊከታተል ይገባል |
| | 10 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ያዘጋጀው የመነሐሪያዎች አስተዳደር መመሪያ በሀገሪቱ ወጥና ተከታታይ ሆኖ ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 11 | የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች(አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣...) ምቹ አገልግሎት (ለአካል ጉዳተኛ ቅድሚያ የመስጠት ህግ ፣በተሽከርካሪው ውስጥ ተሳፍረው ሲሄዱ ሲደክማቸው የሚርፉበት ቦታ፣የመፀዳጃና የተለያዩ መስተንግዶ አገልግሎት...) ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 12 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች(አካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ ህፃናት፣...) ምቹ አገልግሎት መሰጠቱን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 13 | የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ፍላጎት ከፍተኛ በሚሆንባቸው ወቅቶች አገልግሎት አሰጣጡ ባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 14 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ ልዩ እና አስገዳጅ ጉዳዮች ሲያጋጥማቸው የዘረጋውን የአሰራር ስርአት ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 15 | ባለስልጣን መ/ቤቱ በሕ/ትራ/አገልግሎት አሰጣጡ ላይ የተገልጋዬች አስተያየት የሚሰጡበት መድረክ ሊያመቻች ይገባል፡፡ |
| | 16 | ባለስልጣን መ/ቤቱ በሕ/ትራ/አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ከተገልጋዬች የተሰጠውን አስተያየት በግብአትነት ተጠቅሞ ማሻሻዮችን ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 17 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የማህበራት ፈቃድ አሰጣጥ ባወጣው መመሪያ መሰረት ተግባራዊ መደረጉን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | 18 | የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሰጡ የተመደቡ ተሽከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት ደህንነቱ የተጠበቀና ምቾት ያለው አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 19 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕ/ትራ/ማህበራት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ብቃታቸውን በመለየት የደረጃ አሰጣጡ በየጊዜው እንዲፈተሽና እንዲሻሻል ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 20 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ደረጃ የተሰጣቸው የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች በሙሉ ለደረጃው የተቀመጠውን ቀለም መቀባታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 21 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት የሚሰጡ ተሸከርካሪዎች በተሰጣቸው ደረጃ መሰረት አገልግሎት መስጠታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 22 | መናኽሪያ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ጫኝና አውራጅ ሰራተኞች የሙያ ብቃትና የስነ ምግባር ማሻሻያ ስልጠና ሊሰጥ ይገባል፡፡ |
| | 23 | ባለስልጣን መ/ቤቱ—የህዝብ ማመላለሻ ተሸከርካሪዎች ሊሄዱበት የሚገባው የፍጥነት ወሰን ሊኖርና ተግባራዊ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| 2. ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሥምሪት በቁጠባ ብቃት ባለውና ውጤታማ በሆነ መልኩ እያከናወነ መሆኑን መገምገም፣ | 24 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ሥምሪትን ለመግታት የሚያስችል የወጡ የአሰራር ደንቦችና መመሪያዎችን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 25 | ባለስልጣን መ/ቤቱ በቀን የሚፈፀሙ ሕገወጥ ስምሪትንና የለሊት ጉዞ ለማስቀም የወጡ ደንቦችና የአሰራር መመሪያዎች በሁሉም ክልሎችና የባለድርሻ አካላት ተግባራዊ መሆኑን ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 26 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ለተሸከርካሪ ማህበራት የሚሰጡት የመናኸሪያ መውጫ ሰነድ የተሟላ ይዘት ያለው ፣ በህትመት መልክ የተዘጋጀ ፣ተከታታይ ቁጥር ያለውና በባለስልጣን መ/ቤቱ ተመዝግቦ የተያዘ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ |
| | 27 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ከመደበኛ መርሃ ግብር ውጪ፣ (ከአገልግሎት መስጫ መናኸሪያ ውጪ) ህገ ወጥ ስምሪትን እንዲፈፀም ተሳትፎ ባደረገ ሕገወጥ አካል ላይ በመመሪያው መሰረት የቅጣት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 28 | ባለሥልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ ድርጊቶችን እንዲፈፀሙ በሚተባበሩ አስፈፃሚ ሰራተኞች ላይ ክትትል በማድረግ ወጥ የሆነና አስተማሪ ሊሆን የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| 3. ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀልጣፋ አገር አቀፍ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና የልውውጥ ሥርዓት የዘረጋ፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደረፈ መሆኑን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት የሚሰራበት የአሰራር ስርአት የዘረጋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ | 29 | ባለስልጣን መ/ቤቱ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በአገር አቀፍ ደረጃ የትራንስፖርት መረጃ አያያዝና ልውውጥ ለማከናወን የሚያስችል እንዲሁም ወቅታዊና ጥራቱን የጠበቀ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 30 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕገ-ወጥ ትራንስፖርት ድርጊቶችን በአይነት፣ በውጤትና ደረጃቸውን በመለየት መረጃ አደራጅቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ |
| | 31 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የባለ ድርሻ አካላትን ግንዛቤ ለማሳደግ የህዝብ ትራንስፖርት ደንቦች መመሪያዎች፣ መለኪያ መስፈርቶች ፣ስታንዳርዶች፣ የተለያዩ ጥናቶች ፣ የስራ እቅዶች የመሳሰሉትን ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተጠናከረ መልኩ ሊሰጥና ተግባራዊነቱት ሊከታተል ይገባል፡፡ |
| | 32 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕገ-ወጥ ትራንስፖርት ድርጊቶችን ለመከላከል ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረክ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡ |
| | 33 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የሕገ-ወጥ ትራንስፖርት ድርጊቶችን ለመከላከል የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተን እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ባደረገው ውይይት ውጤት መሰረት የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ |
| | 34 | ባለስልጣን መ/ቤቱ የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጡ ወጥ የሆነ የትራንስፖርት አሰራር ስርዓት እንዲኖረው ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት ይኖርበታል፡፡ |
| | 35 | ባለስልጣን መ/ቤቱ ሕገ-ወጥ የትራንስፖርት አገልግሎት ተግባርን ለመግታት የቁጥጥር ስርአት በመዘርጋት ከቅርንጫፍና ከክልል የትራንስፖርት ቢሮዎች ጋር በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡ |